የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ – መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 2
Addis Ababa 20th September, 2004

## ማውጫ

"የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ቻርተር) ቁጥር ፩፻፲፪/፲፱፻፺፯ ዓ·ም
የጎንደር ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋሚያ የወጣ ደንብ....... ገጽ ፪ሺ፱፻፮

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 112/2004
"Council of Ministers Charter Regulation Establishing
Gonder University .................................. Page 2906

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ቻርተር) ቁጥር ፩፻፲፪/፲፱፻፺፯ የጎንደር ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ቻርተር)

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፰ መሠረት ይህን ደንብ (ቻርተር) አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ቻርተር "የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ቻርተር) ቁጥር ፩፻፲፪/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ቻርተር ውስጥ ፣ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣

፩· "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርተ አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ ነው።

፪· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፵፯ ፩(፫) የተጠቀሰው ክልል ነው።

፫· "መንግሥት" ፣ "ሚኒስቴር"፣ "ሚኒስትር"፣ ቦርድ" ፣ "ሴኔት"፣ "የአካዳሚክ ሠራተኛ"፣ "ፈንድ" ፣ "ድርጅት"፣ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋም" የሚሉ ቃላት በአዋጅ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል።

## *COUNCIL OF MINISTERS CHARTER REGULATIONS NO.112/2004 COUNCIL OF MINISTER CHARTER REGULATIONS ESTABLISHING GONDER UNIVERSITY*

*This Charter Regulations is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Art. 8 of Higher Education Proclamtion No. 351/2003*

### *PART ONE*
### *GENERAL*

1. *Short Title*

   This Charter may be cited as the "Gonder University Establishing Council of Ministers Regulation Charter No. 112/2004

2. *Definitions*

   In this Charter unless the context requires otherwise:

   1) "Proclamtion" means Higher Education Proclamation No. 351/2003
   2) "Region" means a region provided under Article 47(1)(3) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.
   3) "Government", "Ministry", "Minister", "Board", "Senate", "Academic Staff", "Fund" "Enterprise" "Higher Education Institution" shall have the definitions given in the Proclamation.

ያንዱ ዋጋ 4.40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

## ክፍል ሁለት
## የዩኒቨርሲቲው መቋቋምና ዓላማ

፫· መቋቋምና ተጠሪነት

፩· ጎንደር ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" ተብሎ የሚጠራ) ራሱን የቻለና የሕግ ሰውነት ያለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ቻርተር ተቋቁሟል።

፪· ዩኒቨርሲቲው በሥሩ የሚከተሉት ተቋማትንና ፋካልቲ ዎችን እና ትምህርት ቤቶችን ያካትታል፦

ሀ) የህክምናና ጤና ሣይንን ኮሌጅ

ለ) የሳይንስ ፋኩልቲ

ሐ) የኢኮኖሚክስ ፋኩልቲ

መ) የማህበራዊ ሣይንስ፣ ሁማኒቲስና ቢዝነስ ፋኩልቲ

ሠ) የእንስሳት ህክምና ፋኩልቲ

ረ) የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ሰ) ወደፊት በቦርዱና በሚኒስቴሩ የሚቋቋሙ ሌሎች ፋኩልቲዎች ፣ ኮሌጆችና ተቋማት

፫· ዩኒቨርሲቲው ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል።

፬· ዓላማ

ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

፩· ሀገሪቱን በተለያዩ ሙያዎች ሊያገለግል የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት ማፍራት ፣

፪· የዘር፣ የሃይማኖት ፣ የፆታ ፣ የፖለቲካና የመሳሰሉት ልዩነቶች የማይደረግበት የከፍተኛ ትምህርት አገል ግሎት መስጠት፣

፫· ሚዛናዊ የሆነ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሥርጭት እንዲኖር ማድረግ፣

፬· ችግር ፈቺ የሆነና የሀገሪቱን እምቅ ሃብት ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ትምህርታዊና ተቋማዊ ሥርዓት መዘርጋት እና ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

፭· ከሀገሪቱ እና ከክልሉ ፍላጎት እና ዕድገት ጋር የተጣጣመ የከፍተኛ ትምህርት እና የህብረተሰብ አገልግሎት መስጠት፣

፮/ የዩኒቨርሲቲውን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት መዘርጋት፣

፯· በአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚመለከተውን ተሳትፎን ማረጋገጥ፣ የአሳታፊነት ባህልን መፍጠርና ማሣደግ፣

፰· በሰዎች መካከል መከባበር፣ መቻቻልና አብሮ የመኖር ባህል እንዲጎለብትና እንዲሰርፅ ማድረግ፣

፭· ሥልጣንና ተግባር

ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩· ፋኩልቲዎች፣ ኮሌጆችና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ተቋሞች አቋቁሞ የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ፕሮግራም መቀየስና ሥራ ማካሄድ፣

፪· የምስክር ወረቀት ፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ የአካዳሚክ ሽልማቶችን መስጠት እንዲሁም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች የአካዳሚክ ሜዳይ ሽልማትና ማዕረግ መስጠት፣

፫· ለሃገር ዕድገት ቅድሚያ በሚሰጥባቸው መስኮች ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

፬· ሴሚናሮች፣ ዓውደ ጥናቶችና ሲምፖዚየሞችን ማዘጋ ጀትና ማካሄድ፣

፭· በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ እኅት ዩኒቨርስ ቲዎች፣ የምርምር ተቋሞችና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አካላት ጋር ግንኙነት መመሥረት፣

፮· የማማከር ፣ የሥልጠናና ሌሎች አገልግሎቶች ለህብረ ተሰቡ፣ ለክልል መስተዳድሮችና ለፌዴራል መንግስት በአግባቡ መስጠት፣

## PART TWO
## ESTABLISHMENT OF THE UNIVERSITY AND ITS OBJECTIVE

3. Establishment and Accountability
   1) There is hereby established the University of Gonder (herein after referred to as "the University") as an autonomous higher education institution having its own legal personality.
   2) The University shall comprise the following institutions, faculties and schools.
      (a) College of Medicine and Health Sciences
      (b) Faculty of Applied Sciences
      (c) Faculty of Economics
      (d) Faculty of Social Sciences, Humanities and Business
      (e) Faculty of Veterinary Medicine
      (f) School of Graduate Studies
      (g) Other Faculties, Colleges and Institutes to be established by the board and the Ministry
   3) The University shall be accountable to the Ministry of Education.
4. *Objective*

   The University shall have the following objectives
   1) provides skilled manpower in quantity and quality that will serve the country in different professions.
   2) expands higher education services that are free from any descrimination on the gounds of race, religion, sex, politics and other similar grounds
   3) lays down problem sloving educational system that enables to utilize potential resources of the country and undertake study and research
   4) provides higher education and community services that are compatible with the needs and development of the country
   5) lays down an institutional system that ensures the accountability of the institution
   6) ensure the participation of all those concerned bodies in administration decision making, create and promote participation culture
   7) makes efforts to develop and disseminate the culture of respect, tolerance and living together among people.
5. *Power and Duties*

   The University shall have the following powers and duties:
   1) to implement undergraduate and postgraduate programs establish and run colleges, faculties, schools, institutes and other academic and rersearch units;
   2) to confer academic certificates, diplomas degrees and other academic awards, and to confer academic titles and medals for those who have made immense contributions;
   3) to undertake relevant studies and research that contributes to the development of the country;
   4) to organize and conduct seminars, workshops and symposia;
   5) to establish relations with different bodies including local and foreign sister universities, research institutions, and other organizations having similar objectives;
   6) to provide appropriate consultancy, special training and other services to the community, local governments and the Federal Government at large;

፯· የትምህርት መጽሔቶችና ጋዜጦች ማቋቋምና ማሠራጨት፣
፰· የማንኛውንም ንብረት ባለቤት የመሆን፣
፱/ ከሶስተኛ ወገን ጋር ውል የመፈራረም፣
፲· በሥሙ የመክሰስና የመከሰስ፣
፲፩· ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢ ክፍያ የማስከፈል፣
፲፪· የገቢ ፈንድ እና የገቢ ማመንጫ ድርጅት ማቋቋም ማስተዳደር፣
፲፫· የዩኒቨርሲቲውን ዓላማ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

፮· ነጻነትና ተጠያቂነት

፩· በቦርዱ የውስጥ ደንቦችና በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ነፃነትና ተጠያቂነት በሚከተሉት ላይ ይኖረዋል።
ሀ) የሲቪል ሰርቪስ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የተቋሙ ሠራተኞች አስተዳደር፣ ቅጥር፣ ዕድገት ፣ እገዳና ሌሎች ጉዳዮችን መፈጸም፣
ለ) የኢትዮጵያን የፋይናንስ አስተዳደር ህግ በመንተራስ በፋይናንስ አስተዳደር፣ በውስጡ ላሉ አካላት በጀት የማከፋፈልና በአግባቡ የመጠቀም፣
ሐ) የሃገሪቱን እና የዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በጠበቀ መልኩ ሥርዓት ትምህርት የመገምገምና የማሻሻል፣
መ) የግልፅነትና ተጠያቂነት መርህ የተከተለ የምርምር ስትራቴጂ መንደፍና ማስፈጸም፣
ሠ) የሲቪል ሰርቪስ መርሆዎችን በመመርኮዝ የውስጥ አደረጃጀትን የመወሰን፣
ረ) የትምህርት፣ የምርምርና የህብረተሰብ አገልግሎት ኃላፊነቱን ለመወጣት ከሀገር ውስጥና ከዉጪ ሀገር ዩኒቨርስቲዎች ጋር የትብብር ግንኙነት መፍጠር
ሰ) የገቢ ማመንጫ ድርጅትን ማቋቋምና ገቢዎቹን የመጠቀም፣

፪· በህግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው ዕውነትን ለመሻት ፣ ዕውቀትን ለማበልጸግ እንዲሁም ውጤቱን ለማሠራጨት የመማር፣ ማስተማር እና ምርምር ነፃነት ይኖረዋል።

፫· የዩኒቨርሲቲው ተጠያቂነት በተለይ፤
ሀ) የሚያካሂዳቸው የትምህርትና ምርምር ፕሮግራሞች ከሃገር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የተገኙ መሆናቸው፣
ለ) ለመንግስት ፕሮግራሞች ቅድሚያ መስጠቱንና ከሃገራዊ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡ መሆናቸውን፣
(ሐ) አጠቃላይ አሠራሩ በግልጽነትና በአሳታፊነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን፣
መ) የበጀትና ሃብት አደላደሉና አጠቃቀሙ ወጪ ቆጣቢና ለህዝብ ኃላፊነትን የሚያረጋግጥ መሆኑን፣
ሠ) የመማር፣ ማስተማርና የምርምር ሥራዎች ተቋማዊ ሆነው በግልጽ የሚከናወኑ መሆኑን፣
ረ) ዩኒቨርሲቲውና የተቋሙ ማኅበረሰብ በሚያስመዘግቡት የጥራትና ተገቢነት ውጤት የሚለኩ መሆኑን፣
ሰ) ማንኛውም በማስተማር፣ በመመራመር በማስተዳደርና በመምራት ኃላፊነት ላይ ያለ የተቋሙ ባልደረባ በተናጠልም ሆነ በጋራ ለተጠሪው አካልና ለህብረተሰብ ተጠያቂነት ያለው መሆኑ፣
በማረጋገጥ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

፯· የመረጃ ልውውጥ

፩· ቦርዱ በሚያወጣው የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መመሪያ መሠረት ከግል ተቋማት፣ ከመንግስታዊ ተቋማት እና ከሌሎች አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል።

7) to establish and publish academic journals and newsletters;
8) to own property;
9) to enter into contracts;
10) to use and be used in its own name;
11) to levy appropriately for the services it is providing;
12) to establish and administer income generartion enterprise and income fund;
13) to carry out such other activities as are necessary for the attainment of its objectives;

6. *Autonomy and Accountability*

1) Subject to internal regulations of the Board and provisions of other laws, the university shall particularly have administrative autonomy and accountability in the following:
(a) impliment the administration of personnel, employment, promotion and other matters of the university staff according to the Principle of Civil Service;
(b) administer finance, allocate and utilize budget to its internal units on the basis of the Financial Law of Ethiopia;
(c) Curriculum review and development in line with national guiselines and international standards;
(d) Formulating research strategy and conducting same on the priniciples of transparency and accountability;
(e) determining internal organization on the principles of the Civil Service Commission;
(f) establishing relation with local and international institutions for the advancement of its academic, research, community service duties;
(g) establishing income generating enterprise and duse the earned-incomes;

2) Subject to limitation provided by other laws, the University shall have academic and ressearch freedom to search for truth, cultivate and advance knowledge, and disseminate the same

3) The University shall have accountability, in particular, with respect to
(a) ensuring that all educational and research programs emanate from the counctry's strategies and policies.
(b) ensuring that priorities are given to government programs and are relevant to the country's situations,
(c) ensuring that the allocation and utilization of budget and resource are based on cost effectiveness and responsibilty to the public,
(d) ensuring that all teaching-learning and research activities are institutionalized and transparent,
(e) ensuring that the university staff are evaluated, individualy and severally, with result commensurate with quality and relevance standards
(f) ensuring that any member of the institutions in responsibilities of teaching, research, administration and leadership is accountable to the public and the body to which it is accountable individually or collectively.

7. *Information Exchange*

1) There shal be an exchange of information between private and public institutions, as well as other bodies and the University as per the internal regulation of the board.

፪· ዩኒቨርሲቲው ማንኛውም ከትምህርት ጋር የተያዘ ምርምር የሚሠራ ሠራተኛ ወይም ተማሪ ጥያቄ ሲያቀርብለት መረጃ ይሰጣል ወይም መረጃ እንዲያገኝ ያደርጋል።

፫· የምርምርና ጥናት ጽሑፎች ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ፣ ተማራማሪዎችና ሌሎች ተጠቃሚዎች በሙሉ እንዲደርሱ የሚደረጉ መሆን አለባቸው።

፰· ጥናትና ምርምር

፩· የጥናትና ምርምር ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው አደረጃጀት በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ደንብና የአስተዳደር መዋቅር የሚወሰን ሆኖ የሚከተሉት መስፈርቶች ይኖሩታል።

ሀ) የዩኒቨርሲቲው የምርምር ተግባራት በአካዳሚክና ምርምር ምክትል ፕሬዚዳንት ይመራል።

ለ) ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምርምር ተቋማት ሊከፍት ይችላል።

ሐ) ዩኒቨርሲቲው ለሚያከናውነው ምርምርና ጥናት በቂ ገንዘብ ማፈላለግ፣ መመደብና በሥራ ላይ ማዋል ይኖርበታል።

መ) ዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥራን የሚሠሩ ተመራማሪዎችና የምርምር ረዳቶች በግል ወይም በጋራ ቅጥር ሊቀጥር ይችላል።

ሠ) ዩኒቨርሲቲው የሚያካሂዳቸው ምርምሮች አግባብነት ካላቸው ከሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር ሊሆን ይችላል።

፪· የዩኒቨርሲቲው የጥናትና ምርምር ርዕስ አመራረጥ፣ የበጀት አጠቃቀምና የሃብት አያያዝ፣ እንዲሁም የምርምር አፈጻጸም ግልጽና ተጠያቂነት መርሆዎችን የተከተለ ይሆናል።

ክፍል ሦስት

ስለ ዩኒቨርሲቲው ፖሊሲና የሥራ አስፈጻሚ አካላት

፱· ስለዩኒቨርሲቲው ቦርድ

፩· የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በሚኒስቴሩ የሚሰየም ሰብሳቢ ይኖረዋል።

፪· ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

| | |
|---|---|
| ሀ) የትምህርት ሚኒስቴር | አባል |
| ለ) የፌዴራል መንግስት ተወካይ (አንድ) | አባል |
| ሐ) የክልል መንግስት ተወካዮች (አራት) | አባል |
| መ) ታዋቂ ግለሰብ | አባል |
| ሠ) ሌሎች በቦርዱ የሚሰየሙ አባላት | አባል |
| ረ) የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት | አባል እና ጸሐፊ |

፫· በቦርዱ የሚሰየሙ አባላት ለልማት አስተዋጽኦ ያደረጉ የዩኒቨርሲቲው አገልግሎት ተጠቃሚዎች መሆን አለባቸው።

፬· ቦርዱ በአዋጅ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፲· የዩኒቨርሲቲው ሴኔት

ሴኔቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

| | |
|---|---|
| ፩· የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት | ሰብሳቢ |
| ፪· የዩኒቨርሲቲው ም/ፕሬዚዳንቶች | አባላት |
| ፫· አካዳሚክ ፕሮግራም ኃላፊ | አባል |
| ፬· የፋኩልቲ፣ የኢንስቲትዩት፣ የት/ቤቶችና ኮሌጆች ዲኖች | አባላት |
| ፭· የህዝብና ውጭ ግንኙነት ኃላፊ | አባል |
| ፮· የሆስፒታል ዳይሬክተር | |
| ፯· የዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር | አባል |
| ፰· የዩኒቨርሲቲው የቤተመጻሕፍት ኃላፊ | አባል |

2) The University has the duty, up on request, to provide a worker, a student or any other body who undertakes research relating to education with information or assist to have access thereto.

3) Research and studies documents shall be made available to all students, researchers and other beneficiaries of the University.

8. *Studies and Research*

1) Particulars on organization necessary to conduct a research work shall be provided in accordance with internal regulations of the University and is based on the following requirements:

(a) The research is led by Academic and Research Vice President

(b) The University may open research institute when it finds necessary

(c) The University shall solicit and allocate sufficient fund for research and study it, conducts and utilizes it for the purpose intended;

(d) The University may employ researchers and their assistants by joint appointmentship;

(e) The University may undertake cooperative research with relevant organizations.

2) The University research and studies projects, their selection, budget utilization and resource ownership as well as implemetation of the same shall be transparent and accountable.

PART THREE

THE UNIVERSITY EXECUTIVE BODIES

9. *The University Board*

1) The Board shall have a chairperson appointed by the Ministry

2) The Board shall have members consisting of:

(a) Ministry of Education .......................... member

(b) One representative of Federal Government- .......................................................... member

(c) Four representatives of Regional Government- ..........................................................members

(d) A renowed and meritorious person ........ member

(e) Other members as determined by the Board- .......................................................... member

(f) President of the University............ member and secretary

3) Members assigned by the Board shall have positive contributions to development and shall be beneficiaries of the service rendered by the University.

4) The Board shall have duties and responsibilities given to it in the Proclamtion.

10. *The University Senate*

The senate shall be accountable to the University president and have the following members:

1) President of the University ...................Chairperson

2) Vice-President of the University................ member

3) Academic Programs Officer........................ member

4) Deans of Faculties, Institutes, Schools & Colleges- ..........................................................members

5)Public and External Relations Officer............ member

6) Hospital Director ........................................ member

7) Registrar of the University .........member&secretary

8) Head Librarian of the University ................ member

፱· የተማሪዎች ዲን ........ አባል

፲· የአካዳሚክ ሠራተኞች ሁለት ተወካዮች ........ አባላት

፲፩· ሁለት የተማሪዎች ተወካዮች ........ አባላት

፲፪· የዩኒቨርሲቲው የሴቶች ጉዳይ ተወካይ ........ አባል

፲፫· የምርምርና ህትመት ኃላፊ ........ አባል

፲፬· ቦርዱ የሚሰይማቸው አግባብነት ያላቸው ሌሎች ኃላፊዎች ........ አባላት

፲፩· የሴኔቱ ሥልጣንና ተግባር

በአዋጁ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሴኔቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩· በቦርዱ የሚወጡ አጠቃላይ መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣

፪· የተማሪዎች አቀባበልን፣ የትምህርት ደረጃ አወሳሰን የዲሲፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት፣ በዚህ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መመርመር፣

፫· አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥና ደረጃዎች አቅጣጫዎችን መወሰን፣

፬· በህግና በቦርዱ የሚወጡ ፖሊሲዎችን መሠረት በማድረግ በተለይ በተማሪዎች አስተዳደር ፣ የዩኒቨርሲቲው የትምህርት ነክ ጉዳዮች፣ የትምህርት ኃላፊዎች የምርጫ ሥነ-ሥርዓት፣ የአካዳሚክ ሠራተኞች ቅጥር፣ ዕድገት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ዲሲፒሊን ፣ ደመወዝ በሚመለከት መመሪያ ማውጣት፣

፭· የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለቦርዱ ሃሣብ ማቅረብ፣

፮· የረዳትና የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግን መስጠት፣

፯· የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር መመርመርና ማስጽደቅ፣

፰· የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መወሰን፣

፱· ፕሬዚዳንቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚጠራው ስብሰባ እንደተጠበቀ ሆኖ በየሩብ ዓመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ መሰብሰብ፣

፲· ተግባሩን ለሌሎች የዩኒቨርሲቲው አካላትና ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ማስተላለፍ፣

፲፩· በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን።

፲፪· ስለ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንቶች

፩· የዩኒቨርሲቲው እጩ ፕሬዚዳንት ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች የተመሰከረለት የአካዳሚክና አስተዳደር ብቃት እንዲሁም መልካም ሥነ-ምግባር ሊኖራቸው ይገባል።

፪· ዩኒቨርሲቲው ለፕሬዚዳንቱ ተጠሪ የሆኑ ሦስት ም/ፕሬዚዳንቶች ይኖሩታል።

፫· የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንቶች የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።

፬· የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በአዋጁ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፲፫· የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር

፩· የአካዳሚክና ምርምር ም/ፕሬዚዳንት

ሀ) የዩኒቨርሲቲውን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚዳንት ያማክራል ፣ ይረዳል፣

ለ) በቦርዱና በሴኔቱ የተላለፉ ውሣኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ በማዋል ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ ክፍሎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ) የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በማይኖርበት ጊዜ ተተክቶ ዩኒቨርሲቲውን ይመራል፣ ያስተባብራል፣

9) Student's Dean .......................................... member
10) Two Academic Staff' Representative ......... memebr
11) Two Students' Represntative ...................... member
12) Head or Representative of Gender Mainstreaming Office ........................................................ member
13) Head of Research and Publications............members
14) Other appropriate members of the University to be assigned by the Board ................................members

11. *Powers and Duties of the senate*

Subject to the provisions of the Proclamation, the Senate shall have the following powers and duties:

1) to implement directives issued by the board
2) to set criteria for admission of students, determination of academic standards and graduation, and regulate disciplinary matters; to examine and decide on petitions relating to same;
3) to determine the general standards and directions of conducting of examinations
4) to issue specific directives on the basis of law and policies drawn up by the Board particularly on student administration, academic matters, procedure for selection of academic heads, employment of academic staff, promotion, fringe benefits, discipline and salary;
5) to propose promotion of professorship to the Board
6) to award academic promotion of associate and assistant professorships;
7) to examine and approve the employment of academic staff of the University;
8) to issue its own meeting procedures and internal regulations;
9) subject to the condition where the president may call a meeting where he deems necessary, to have at least one meeting each quarter;
10) to delegate its duties to others university bodies and standing or ad-hoc committees;
11) to perform such other activities, as may be assigned to it by the Board and/or the president.

12. *President and Vice-President of the University*

1) The candidate presidents of the university shall have commendable academic and managerial ability as well as ethics;
2) There shall be three vice presidents of the university accountable to the president;
3) The term of office of the University president and Vice-president shall be five year;
4) The University President shall have duties and responsibilities as provided in the Proclamation.

13. *Vice-Presidents and their Powers and Duties*

1) The University Academic and Research Vice-President shall
   (a) consult and assist the President regarding the powers and duties of the university
   (b) direct and supervise the activities of the university organs accountable to it upon implementation of the decisions and directives issued by the Board and Senate
   (c) In the absence of the president, direct and coordinate the activities of the university on behalf of the president

መ) የትምህርት ማዕከላትን እንደፋኩልቲ፣ ኮሌጅ፣ ተቋም፣ ትምህርት ቤት እና ተከታታይ ትምህርት ክፍሎችን ሥራ ያቅዳል፣ ይመራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣

ሠ) የምርምር እና ጥናት እንቅስቃሴዎችን ያቅዳል፣ ይመራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣

ረ) የዩኒቨርሲቲውን መጻሕፍት ቤት፣ ሬጅስትራር ጽሕፈት ቤትና ሌሎች በሥሩ ያሉትን ክፍሎች ይመራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣

ሰ) ብሔራዊና ዓለምአቀፍ ግንኙነቶችንና ትብብሮችን ያፈላልጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣

ሸ) በሥራ ያሉ ክፍሎችን የሥራ አፈጻጸም፣ በጀት ክፍፍልና አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ሪፖርት ለፕሬዚዳንት ያቀርባል፣

ቀ) በቦርዱ፣ በሴኔቱና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራት ያከናውናል።

፪· የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ም/ፕሬዚዳንት፣

ሀ) የዩኒቨርሲቲውን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚዳንት ያማክራል፣ ይረዳል፣

ለ) ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ) የተማሪዎች አገልግሎትን፣ የአስተዳደርና የፋይናንስ ሥራ ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

መ) በቦርድና በሴኔቱ የተሰጡ ውሣኔዎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሠ) የተቋሙን አስተዳደርና ማኔጅመንት አቅም ለማሻሻል ከብሔራዊና ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

ረ) የሥራ አፈጻጸም፣ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም እንዲሁም የሌሎች እንቅስቃሴችን ሪፖርት ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፣

ሰ) በቦርዱ፣ በሴኔቱና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራት ያከናውናል።

፫· የዩኒቨርሲቲው የቢዝነስና ልማት ም/ፕሬዚዳንት፣

ሀ) የዩኒቨርሲቲውን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚዳንት ያማክራል፣ ይረዳል፣

ለ) ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የዩኒቨርሲቲውን ክፍሎች ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ) በቦርድና በሴኔቱ የተላለፉ ውሣኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣

መ) የገቢ ማመንጫ ድርጅቶችንና የዩኒቨርሲቲውን የቢዝነስ ክፍሎች በተመለከተ ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ የሥራ ባህልን ያጎለብታል፣

ሠ) በዩኒቨርሲቲው አዳዲስ የቢዝነስ ሃሣቦችንና ልማትን ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ረ) የዩኒቨርሲቲውን አዳዲስ የልማትና የማስፋፋት የካፒታል ኢንቨስትመንቶችን ያቅዳል፣ ያስተዳድራል፣

ሰ) ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የተገናኙና እርሱን የሚመለከቱ ስምምነቶችና ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሸ) ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችንና ትብብሮችን ያፈላልጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣

ቀ) በሥሩ የሚገኙትን አካላት የሥራ አፈጻጸሙን፣ የበጀት ድልድልና አጠቃቀምን በተመለከተ ሪፖርት ያቀርባል፣

(d) plan, lead supervise academic activities of the University in its faculties, institutes, schools and continuing education programs

(e) plan, lead and supervise research and studies activities, agreements and projects of the University

(f) lead and supervise the library, registrar and other organs of the University,which are directly accountable to it.

(g) solicit national and international links and partnerships, and follow their implementation

(h) report on activity performance, budget allocation and utilization and other activities of the units under it to the president.

(i) Carry out such other activities which may be specifically entrusted to it by the Board, the Senate or the President.

2) The University Administrative Vice-President shall

(a) consult and assist the President regarding the powers and duties of the University

(b) direct and supervise the activities of the University organs accountable to it

(c) direct and supervise the Unversity students services, financial, administrative and support services

(d) implement the decisions and directives issued by the Board, or Senate

(e) solicit and administer national and international partnerships to improve the administrative and mangement capacity of the institution

(f) report on activity performance, budget allocation and utilization and other activities of the units under it to the president.

(g) undertake other duties given to it by the Board, the Senae or the President

3) The University Development and Business Vice-President

(a) consult and assist the President regarding the powers and duties of the University

(b) direct and supervise the activities of the University organs accountable to it

(c) implement the decisions and directives issued by the Board, or Senate,

(d) plan, direct and supervise entrepreneurial enterprises, and business units of the University, and create and entrepreneurial culture

(e) plan, program, direct and supervise new ventures and developments in the University, and outsourcing of the facilities and services,

(f) plan, program and manage capital invetments of the University that are related to new developments and expansions.

(g) direct, lead and supervise implementation of agreements and projects related to its domain with other organizations,

(h) actively solicit national and international links & partnerships, and execute the same;

(i) report on activity performance budget allocation and utilization and other activities of the units under it,

በ) የቢዝነስና የስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ያቀርባል፣

ረ) ሌሎች ከቦርድ፣ ከሴኔቱና ከፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

፬· የህክምናና ጤና ኮሌጅ ለአካዳሚክና ምርምር ምክትል ፕሬዚዳንት ተጠሪ በሆነና የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት በሚኖሩት ተባባሪ ምክትል ፕሬዚዳንት ሊመራ ይችላል።

ሀ) የዩኒቨርሲቲውን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ የዩኒቨርሲቲውን ምክትል ፕሬዚዳንት ያማክራል፣ ይረዳል፣

ለ) የህክምናና ጤና ኮሌጅን ትምህርት፣ ምርምርና አገልግሎት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ) የሆስፒታሉን ታካሚዎችና ጤና አጠባበቅ አገልግሎት እንዲሁም የአስተዳደርና ፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

መ) ለህብረተሰብ ተኮር የተግባር ትምህርት የሚያገለግሉ ከተቋሙ ውጭ ያሉ የማሠልጠኛ ጣቢያዎችን እንቅስቃሴ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሠ) ከብሔራዊና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ግንኙነትና ትብብር ያፈላልጋል፣

ረ) ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ ክፍሎችን የሥራ አፈጻጸም፣ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም እንዲሁም የሌሎች እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣

ሰ) የቢዝነስና የስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣

ሸ) በቦርዱ፣ በሴኔቱና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራት ያከናውናል።

፲፬· የአካዳሚክ ኮሚሽን

፩· እያንዳንዱ ፋኩልቲ ኮሌጅ ኢንስቲትዩት እና ትምህርት ቤት ለዲኑ ተጠሪ የሆነ የራሱ አካዳሚክ ኮሚሽን ይኖረዋል።

፪· የአካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

ሀ) የፋኩልቲ፣ ኮሌጅ፣ ኢንስቲትዩት ወይም ትምህርት ቤት ዲን ................................ ሰብሳቢ

ለ) የፋኩልቲ፣ ኮሌጅ ፣ ት/ቤት ወይም ኢንስቲትዩት ምክትል ዲኖች ካሉ ............ አባላት

ሐ) የትምህርት ክፍሎች ኃላፊዎች ................ አባላት

መ) አንድ የተማሪዎች ተወካይ ....................... አባል

ሠ) በአካዳሚክ ሠራተኞች ጠቅላላ ጉባዔ የተመረጠ አንድ የመምህራን ተወካይ ......... አባል

ረ) የፋኩልቲው የተከታታይ ትምህርት አስተባባሪ ............................................... አባል

ሰ) በኮሚሽኑ የሚመደቡ አግባብነት ያላቸው ኃላፊዎች .................................. አባላት

፫· የዩኒቨርሲቲው ሴኔት የሚያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የአካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ) የፋካልቲውን፣ የኮሌጁን፣ የተቋሙን ወይም የትምህርት ቤቱን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በጀት በማዘጋጀት ይደለድላል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ለ) የሥልጠናና የትምህርት መርሀ ግብሮችን ሥርዓተ ትምህርቶች አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ያጸድቃል፣

ሐ) በሴኔቱ መመሪያ መሠረት የተማሪዎችን ትምህርትና ሥነ-ምግባር የተመለከቱ ዝርዝር መስፈርቶችን ይወስናል፣

መ) ከትምህርት ጋር የተያያዙ ሽልማቶችንና የክብር ዲግሪ እንዲሰጥ ለሴኔቱ ሃሣብ ያቀርባል፣

ሠ) የሌክቸር፣ ረዳት ሌክቸረር፣ ረዳት ምሩቅና ቴክኒክ ረዳቶችን ዕድገት በሴኔቱ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አጣርቶ ይወስናል፣

(j) prepare and submit business and strategic plans,

(k) undertake other duties given to it by the Board, the Senate or the President.

4) The College of Medicine and Health Sciences may be managed by Associate Vice President, accountable to the Vice President for Academic and Research Affairs and having the following duties and responsibilities:

(a) consults and assist the President regarding the powers and duties of the university

(b) Plans, directs and supervises the teaching, research and services of College of Medicine and Health Sciences.

(c) Plan, leads and supervises the activities of patients' and healthcare services of the hospital, their administration and finance

(d) Directs and supervises the activities of the satellite campuses used for community-based practical education

(e) activity solicit national and international links and partnership

(f) report on activity performance, budget allocation and utilization and other activites of the units under it

(g) Prepares and submit business and strategic plans

(h) Discharges such other activities which may be specifically entrusted to it by the Board, the Senate or the President

14. *Academic Commission*

1) Each faculty, College, institute or school shall have an Academic Commission accountable to the Dean.

2) The academic commission shall have the following members:

(a) Deans of the Faculty, College, School or Institute ............................................chairperson

(b) Vice-deans of the faculty, college, school or institute, if any .................................. member

(c) Head of each departments .................. member

(d) One Students' representative............... memebr

(e) One representative of the academic staffsmember

(f) Faculty of Continuing Education Coordination ...................................... member

(g) Appropriate members to be assigned by the commission........................................ member

3) Subject to directives of the Senate, the academic commission shall have the following powers and duties;

(a) Plans activities, prepares and allocates budget within the faculty, college, institute or school and follow the implementation of the same;

(b) submits for approval, by the Senate, curricula of training and educational programs of the institution;

(c) sets criteria for students, related to education and desciplinary matters, with due consideration to directives of the Senate;

(d) recommends to the senate honorary degree awards and education related prize;

(e) examines and determines the award of the academic promotions of lectures, assistant lecturers, graduate assistants and technical assistants, as per the internal regulations of the board;

ረ) የተባባሪና ረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለሴኔቱ አቅርቦ ያጸድቃል፣

ሰ) የአካዳሚክ ሠራተኞች ቅጥርን ይመረምራል፣ የነፃ ትምህርት ዕድልና የምርምርና ሰባቲካል እረፍቶችን ያጸድቃል፣

ሸ) የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓትና የውስጥ ደንብ ይወስናል፣

ቀ) ከሴኔቱ እና ከፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል።

፲፭· የትምህርት ክፍል ጉባዔ

፩· እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል የራሱ ጉባዔ ይኖረዋል።

፪· የትምህርት ክፍል ጉባዔ በትምህርት ክፍሉ ኃላፊ የሚመራ ሆኖ ሁሉንም የሙሉ ጊዜ መምህራንን ያካትታል።

፫· የትምህርት ክፍል ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

ሀ) ተፈላጊ በሆኑና ሰርቲፊኬት ወይም ዲፕሎማ ዲግሪ የሚያሰጡ መርሃ ግብሮችን ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ያስፈጽማል፣

ለ) የትምህርት ክፍሉን ዓመታዊ ዕቅድ በጀትና ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ይመዘገባል፣

ሐ) የትምህርት ክፍሉን የሰው ኃይልና ፋይናንስ ይከታተላል፣

መ) የመምህራንና የተማሪዎችን ግምገማ ክትትል ያከናውናል፣ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ይወስናል፣

ሠ) ፈተናዎችንና የአካዳሚክ ግምገማ ሥርዓትን ደረጃ ያወጣል፣ ይከታተላል፣

ረ) የማስተማሪያ ጽሑፎችን አመራረጥና ዝግጅት ይወስናል፣ የመምህራንን የሥራ ጫና ይወስናል፣

ሰ) በሥርዓተ ትምህርትና በመማር ማስተማር ሥርዓት ማሻሻያዎችና ፈጠራዎች እንዲጎለብቱ ሁኔታዎች ያመቻቻል፣

ሸ) የተማሪዎችን ውጤት ያጸድቃል፣

ቀ) ሌሎች በፋካልቲውና በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል።

፲፮· ስለዩኒቨርሲቲው ልዩ ልዩ ክፍሎች የውስጥ ሥልጣን

፩· በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፪ ሥር የተዘረዘሩት እና ሌሎች የዩኒቨርሲቲው አካላት አደረጃጀት ቦርዱ ባጸደቀው መዋቅር መሠረት ይወሰናል።

፪· እያንዳንዱ ፋኩልቲ፣ ተቋም፣ትምህርት ቤት ወይም/እና ኮሌጅ የበጀት ማዕከል ደረጃ ሊኖረው ይችላል፣

፫· እያንዳንዱ የበጀት ማዕከል የራሱን ዕቅድና በጀት ማዘጋጀት፣ የበጀት እና ሃብት አጠቃቀምን መወሰንና ሪፖርት ማዘጋጀት ይኖርበታል።

፲፯· የማኔጅመንት አመራር አሰያየም

በዩኒቨርሲቲው አካላት ውስጥ ያሉ አካላትን ለመምራት የሚታጭ ሰው በተለይ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት።

ሀ) የማኔጅመንት የአስተዳደርና የአመራር ብቃት ያለው፣

ለ) በዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ፣ የምርምርና የኅብረተሰብ አገልግሎት ውስጥ ብቁ ተሳትፎ ያለው፣

ሐ) ሥራዎቹ ውጤት ያሣዩና መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፣

መ) ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን የመተግበርና የማስረጽ ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ያለው፣

(f) recommends to the Senate the award of the academic promotions of assistant and associate professorship;

(g) examines the employment of the academic staff; and decides on the cases of scholarship, research and sabbatical leaves;

(h) issues its own meeting procedures and internal regulations;

(i) performs such other activities as may be assigned to it by the president and the Senate

15. *Department Assembly*

1) Each department in the University shall have Department Assembly

2) Every Department Assembly shall be composed of all fulltime academic staff members of the department and shall be chaired by the Head of the Department.

3) A Department Assembly shall have the following powers and duties:

(a) to submit recommendations to the academic commission on the programmes of studies necessary for obtaining certificates, diplomas or degrees offered by the department courses; and execute same;

(b) prepare the annual plan, budget and reports of the department;

(c) monitor the financial and personnel management of the department;

(d) conduct teachers' and students' appraisal and evaluation; examine complaints thereof,

(e) stadardize and supervise examinations and academic evaluations systems;

(f) determine teaching material selection and preparation to courses, and approve distribution of teaching load to staff members;

(g) support and facilitate quality improvement and innovation in curriculum and learning-teaching systems;

(h) approve students' grade.

(i) undertake such other similar duties assigned by the faculty and the university

16. Internal Autonomy of Organs of the University

1) the establishment and function of the various main organs of the University described in Article 3 Sub-Article 2 of this Charter shall be determined by organizational structure to be approved by the Board;

2) each faculty, institute, school and/or college may have a cost center status.

3) each cost center shall prepare its own action plan, budget, determine the usage of budget and resources and perpare report;

17. *Management and Leaderships Appointment*

The candidate for different positions available in different organs of the University shall meet the following criteria;

(a) managerial administration and leadership competence;

(b) demonstrate ability to effectvely participate in all the academic, rersearch and community services of the University;

(c) demonstrated results and good conduct;

(d) preparedness and commitment for ability to practice and inclucate democratic values.

## ክፍል አራት
## ስለ ዩኒቨርሲቲው ሠራተኞችና ተማሪዎች

፲፰· የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች

፩· ዩኒቨርሲቲው በአዋጁ የተመለከቱት ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፪· ዩኒቨርሲቲው ከሌላ መንግሥታዊ ወይም የግል ተቋም ሠራተኛን በጋራ ቅጥር መቅጠር ይችላል።

፫· የጋራ ቅጥሩ በሁለቱ ተቋማት መካከል በሚደረግ ውለታና በግለሰቡ ስምምነት መሠረት ተግባራዊ ይሆናል።

፬· በጋራ የተቀጠረው ባለሙያ እንደቋሚ መምህር የሚታይ ሆኖ በሕጉ የተመለከቱት ግዴታና መብቶች ይኖሩታል።

፭· የዩኒቨርስቲው ሠራተኞች መብትና ግዴታ በአዋጁ የተመ ለከተው ይሆናል።

፲፱· ስለተማሪዎች መቀበያ መመዘኛ ተማሪዎች

፩· በሌሎች ህጎች ስለመቀበያ መመዘኛ የተደነገገው እንደተ ጠበቀ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው፣

ሀ)ተገቢውን መመዘኛ ላሟሉ ኢትዮጵያውን ያለምንም ልዩነት ክፍት ይሆናል፣

ለ) የኢትዮጵያ የሁለተኛ ደረጃ የመዘጋጃ ትምህርት ወይም ሚኒስቴሩ በሰጠው ግምት ደረጃ ያለው የውጭ ሀገር ሁለተኛ ደረጃን ያጠናቀቀ እና በዩኒቨርሲቲ አቸው የተሰጠውን የመግቢያ መመዘኛ ያሟላ ተማሪን ለቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር ትምህርት ይቀበላል፣

ሐ) የዲፕሎማ (12+2እና 10+3) ደረጃ ያላቸው ተማሪ ዎችን በአድቫንስድ ተማሪነት በቅድመ ምረቃ ይቀበላል፣

መ) የከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃ ትምህርት ያጠና ቀቀና በዩኒቨርሲቲው የተወሰኑ መመዘኛዎችን ያሟላ ተማሪን ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ትምህርት ይቀበላል፣

ሠ) ለሴቶች፣ ለታዳጊ ክልል ብሔረሰብ እንዲሁም ለጎልማሣ ወይም ልምድ ላላቸው ተማሪዎች የተለየ አቀባበል ሥርዓት ሊወሰን ይችላል።

፪· ዩኒቨርሲቲው የሚቀበለው ተማሪ በወጪ መጋራት መርህ መሠረት ያለበትን ግዴታ የሚያሟላ መሆን አለበት።

፫· ዩኒቨርሲቲው የተማሪውን ችሎታ እና የዕውቀት ደረጃ እንዲሁም ክህሎት ለመገምገም የሚያስችል መመዘኛ ያዘጋጃል።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የሚሰጥ መመዘኛ ለተማሪው በተሰጠው ትምህርት ወይም ሥልጠና ይዘት ላይ የተመሠረተ ተከታታይ ምዘና መሆን አለበት፣

፭· መመዘኛው የሚሰጥበት መንገድ በቃል፣ በጽሑፍ፣ በተግ ባርና ሌሎች ሴኔቱ በሚወስንባቸው መንገዶች ሊሆን ይችላል፣

፮· የምዘና ውጤቶች እና የፈተና ወረቀቶችን ለተማሪው መመለስ ወይም በግልጽ ማሳወቅ አለበት።

## ክፍል አምስት
## ስለድርጅትና ፈንድ ፈንድ

፳· ስለ ድርጅቱ መቋቋምና አካላቱ

ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው የቢዝነስና ልማት ምክትል ፕሬዚ ዳንት የሆነ የሚከተሉት አካላት ያሉት የዩኒቨርሲቲው ድርጅት ተቋቁሟል።

ሀ) የምክር አገልግሎት

ለ) የምርት አገልግሎት

ሐ) የፕሮጀክት አገልግሎት

መ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት

ሠ) ወደፊት የሚቋቋሙ ሌሎች አገልግሎቶች

## PART FOUR
## STAFF AND STUDENTS OF THE UNIVERSITY

18. *The University Staff*

1) The University shall have staff as provided in the Proclamation
2) The University may employ a staff of another institution, government or private entities in the form of a joint appointment-ship.
3) The joint appointment-ship is effected upon agreement between the respective employing organization, as well as the consent of the individual
4) The joint-appointee shall be considered as a full time academic staff enjoying all the rights and duties provided in the laws.
5) Duties and responsibilities of University staff shall be as provided in the Proclamation.

19. *Admission of Students*

1) Without prejudice to the provisions of this charter and other relevant laws regarding the requirements of admission of students, the University shall:
   (a) be open to all qualified citizens of Ethiopia and without any discrimination.
   (b) admit, for undergraduate studies, students who have completed Ethiopian preparatory level school education or foreign high school education that has equivalent level as determined by the Ministry, and those who satisfy entrance qualifications assessment of the University;
   (c) admit students with diploma (12+2 and 10+3) as advanced students in its undergraduate programs.
   (d) admit, for post graduate studies, students who have completed heir undergraduate studies and satisfy entrance qualifications set by the University;
   (e) determine special admission procedures, for female students, students from developing regions, adults and expereinced students
2) All students shall fulfill the requirements as provided in the principles of cost sharing.
3) The University shall design an assessment mechanism that enables it to evaluate the ability and level of knowledge as well as skills of its students.
4) The methods of assessment designed in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be based on the content of course or training offered to the student and based on continous assessment.
5) The method of assessment may be oral, written, practical or any other form to be decided by the Senate;
6) The University shall return and notify transparently the results and examination papers to students.

## PART FIVE
## INCOME GENERATION AND FUND

20. *Establishment of Enterprise and Its Units*

An enterprise, accountable to the University Development and Business Vice-President, having the following units is hereby established:

(a) The consultancy service
(b) The production service
(c) The projects service
(d) The information technology service
(e) Other services to be established by the University

**፳፩· የገቢ ምንጭ**

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

፩· ይህ ቻርተር ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከዩኒቨርሲቲው የገቢ ምንጭ አካላት የተገኙ ገቢዎች የድርጅቱ የገቢ ምንጭ ይሆናሉ።

፪· ቻርተሩ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የነበሩ የዩኒቨርሲቲው የገቢ ማመንጫ አካላት በድርጅቱ ሥር ይሆናሉ።

**፳፪· የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ፈቃድ ማግኘትን የመሳሰሉ በሕግ የተደነገጉ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩· የማማከር አገልግሎት መስጠት፣
፪· ላቦራቶሪ ምርመራ ማድረግ
፫· የእርሻ ውጤቶችን ማምረትና ማሠራጨት
፬· የሆስፒታል አገልግሎት
፭· ጥናቶችና ንድፍ ሥራዎችን እና የፕሮጀክት ሰነዶችን ማዘጋጀትና አስተያየት መስጠት፣
፮· ልዩ ፋርማሲዎች
፯· ኢንተርኔት ካፌና ኮምፒዩተር ማዕከል፣
፰· ያሉትን መሣሪያዎችና መገልገያዎች ማከራየት
፱· መጻሕፍትንና የህትመት ውጤቶችን መሸጥ፣
፲· የንብረቶች ባለቤት መሆን፣

**፳፫· የድርጅቱ አስተዳደር**

የድርጅቱ አጠቃላይ አስተዳደር ድርጅቱን፣ አካላቱን የሚመሩ ሰዎች የሚመረጡበት እና የሚተዳደሩበት የድርጅቱ መዋቅር፣ የካፒታሉና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች በቦርዱ ይወሰናሉ።

**፳፬· የድርጅቱ የፋይናንስ መግለጫና የሥራ እንቅስቃሴን ስለማቅረብ**

የድርጅቱ የፋይናንስ መግለጫና የሥራ እንቅስቃሴ የድርጅቱ የበጀት ዓመት ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት የ፫ ወራት ጊዜ ውስጥ በሚመለከተው የድርጅቱ አካል ለቦርዱ መቅረብ አለበት።

**፳፭· ስለ ፈንድ መቋቋም**

ዓላማና የገቢ ምንጩ በአዋጁ የተገለጸው የዩኒቨርሲቲው ፈንድ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

**፳፮· የፈንዱ አካላት**

፩· ፈንዱ፣
ሀ) የፈንዱ አስተዳደር ቦርድና (ከዚህ በኋላ ቦርድ ተብሎ የሚጠራ)
ለ) ሴክሬታሪያት
ይኖረዋል።

፪· ቦርዱ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ይሆናል።

**፳፯· የፈንዱ ቦርድ አባላት**

፩· ቦርዱ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።
፪· የቦርዱ የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።
፫· የቦርዱ አባላት በማናቸውም ሁኔታ ሥራቸውን መሥራት ካልቻሉ በምትካቸው አዲስ አባል ይሰየማል።

**፳፰· የፈንዱ ቦርድ ስልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

፩· የፈንዱ ዓላማዎችን ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል ለአፈጻጸማቸው አስፈላጊውን መመሪያ ያወጣል፣

21. *Powers and Duties of the Enterprise Source of Income*

Without prejudice to the income sources of the enterprise provided by the Proclamation

1) Income generated from income generating units of the university before the coming into effect of this Charter, shall be income of the enterprise.
2) Income generating units of the university established before the coming into force of this charter shall be under the enterprise

22. *Powers and Duties of the Enterprise*

In addition to requirements such as acquiring licenses, in accordance with relevent laws the enterprise has the following powers and duties;

1) Giving consultancy services;
2) Carry out laboratory tests
3) Producing and distributing agricultural products;
4) Hospital Services;
5) Prepare and review of project documents, designs and studies;
6) Special pharmacies;
7) Internet cafes & computer centers;
8) Renting facilities;
9) Sales of books and other published materials;
10) Own property

23. *Managemet of the Enterprise*

The general management of the enterprise, its structure, capital, the election of its managers and other relevant issues shall be decided by the board.

24. *Submission of Enterprise and Activity Report of the Enterprise*

The enterprise, shall, within three months after the end of its fiscal year, submit to the board the financial and activity report of the enterprise.

25. *Establishment of the Fund*

Upon the request of the University and with the approval of the Board or the Ministry a Fund shall be established having aim and source of income as provided by the Proclamation.

26. *Organs of the Fund*

The Fund shall have:

(a) Fund Administration Board (herein referred to as the "Fund Board");
(b) Secretaria;

27. *Members of the Fund Board*

1) The Fund Board shall have members assigned by the President of the University
2) The term of the Board shall be two years
3) In case of absence of any number of members due to any reason, a new member shall be appointed.

28. *Duties and Responsibilities of the Fund Board*

*The board shall have the following duties and responsibilities:*

1) Follows up the implementation of the aims of the fund and issue the necessary directives for the execution of the same

፪· ከልዩ ልዩ የፈንዱ ምንጮች የተገኙ ገቢዎች በተገቢ ሁኔታ ሥራ ላይ መዋላቸውን በተመለከተ በሴክሬታሪያቱ የሚቀርብለትን ሪፖርት መርምሮ ያጸድቃል።

፫· የፈንዱ ገቢዎች በየጊዜው መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል።

፬· ለፈንዱ ዓላማ መሳካት የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

፳፱· የፈንዱ ቦርድ ስብሰባዎች

የቦርዱ ስብሰባዎች የሚካሄዱበት ሁኔታና የድምጽ አሰጣጡ ሥነ – ሥርዓት ቦርዱ በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

፴· የአስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ ሥልጣንና ተግባር

አስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩· ዓመታዊ በጀት፣ የሥራ እንቅስቃሴና የሂሣብ መግለጫ ሪፖርቶችን ለፈንዱ ቦርዱ አቅርቦ ያጸድቃል።

፪· በፈንዱ ድጋፍ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችን ይመረምራል፣ በቦርዱ መመሪያ መሠረት የፕሮጀክቶቹን የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ይፈቅዳል፣

፫· ለፈንዱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታ ዎችን ያጠናል፣

፬· የቦርዱን የሥራ መዛግብት፣ ዘገባዎችና የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎችን ይይዛል፣ የቦርዱ ውሣኔዎች በትክክል መፈጸማ ቸውን ያረጋግጣል፣

፭· በፈንድ ቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል ።

፴፩· የፈንዱ ሴክሬታሪያት ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

የፈንዱ ሴክሬታሪያት ዳይሬክተር ፈንዱን በሚመለከት ጉዳዮች ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴ የተመለከቱትን የሴክሬታሪያቱን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል።

## ክፍል ስድስት
## ስለ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች

፴፪· ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን ቻርተር የሚቃረኑ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

፴፫· የመብትና ግዴታ መተላለፍ

ጎንደር በመባል የሚታወቀው ዩኒቨርሲቲ በዚህ ቻርተር ከመቋቋሙ በፊት ያለው መብትና የነበረበት ግዴታ በዚህ ቻርተር ለዩኒቨርስቲው ተላልፏል።

፴፬· ቻርተሩ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ቻርተር በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

2) Examine reports submitted by the secretariat on the application of different sources of income for their intended purposes and approve it;
3) Ensures that the income of the fund are duly collected;
4) Carries out other activities necessary for the achievement of the aims of the fund

29. *Meetings of the Fund Board*

The time for convening of the meetings of the Board and the procedure voting in the meetings shall be determined by rules and procedures issued by the Fund Board.

30. *Powers and Duties of the Secretariat*

The secretariat shall have the following powers and duties:

1) Prepares annual budgets; activity and financial reports and submit those for the approval to the Fund Board:
2) examines projects prepared and assisted by the fund, and allows the fund for the implementation of the same in accordance with the directives issued by the board;
3) studies additional ways and sources of the finance to be used for the Fund
4) keeps minutes, reports and working papers of the Fund board; follows up the appropriate implementation of directives issued by the Fund Board;
5) execute other duties provided by the board.

31. *Powers and Duties of Director of the Secretariat of the Fund*

The director of the secretariat of the fund shall be accountable to the Fund Board on matters related to the Fund and implement powers and duties of the secretariat provided under Article 30 of this Charter.

## PART SIX
## MISCELLANEOUS

32. *Inapplicable Laws*

Any regulations or directives inconsistent with the provisions of this charter shall not be applicable.

33. *Transfer of Rights and Duties*

This rights and duties of the institute known as Gonder before coming into force of this Charter is hereby transfered to the University.

34. *Effective Date*

This Charter shall enter into force from the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta

Done in Addis Ababa this 20th day of September, 2004)

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA